ክቡራን የዚህ ጉባኤ ተሳታፊዎች!
ክቡራን ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!

ክቡራትና ክቡራን!

ከሁለት ዓመት ከመንፈቅ የእስራት የስቃይና የውጣ ውረድ ጊዜያት በኋላ ዛሬ በዚህ መልኩ ለመገናኘት በመብቃታችን የተሰማኝን ደስታና ኩራት ለዚህ ተግባር ስኬት በታገሉ የአመራር አባላት፣ በጽናት በቆሙ የፓርቲው አባላትና ደጋፊዎች ስም ስገልጽ ለዚህ ላበቃን ፈጣሪ ምሥጋና ይግባው በማለትም ጭምር ነው፡፡

ይህ ሪፖርት በዋናነት አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲያችን ህጋዊ እውቅና አግኝቶ በሀገሪቱ ህግ መሠረት ለመንቀሳቀስ የሚያስችለውን ሁኔታ ለማሟላት አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርግ የተቋቋመው አስተባባሪ ኮሚቴ ዘገባ ነው፡፡ ሆኖም እኛ የጉባኤው ተሳታፊዎች፣ የኢትዮጵያ ህዝብና የአለማቀፍ ህብረተሰብ እንደሚያውቀው አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ከባዶ አልተነሳም፡፡ መነሻ ታሪክ አለው፡፡ ይህ መነሻ ታሪክ የቀድሞው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ታሪክ ነው፡፡ ስለዚህ የቀድሞው ቅንጅትን ታሪክ በዚህ ሪፖርት ውስጥ በአጭሩ ማካተት የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አመጣጥ ታሪክን የተሟላ ያደርገዋል፡፡

በሪፖርቱ ላይ ውይይት በሚደረግበት ጊዜም ትኩረታችን ስለቀድሞው ቅንጅት በተባለው ላይ ሳይሆን አስተባባሪ ኮሚቴው ተቋቁሞ ስራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬው እለት ድረስ የተከናወኑ ተግባራትን አስመልክቶ በተባለው ላይ መሆን አለበት፡፡ ለወደፊት የቀድሞው ቅንጅት ታሪካችንን እያነሳን ከደካማም ሆነ ከጠንካራ ጎናችን ትምህርት የምንቀስምበት ሰፊ ጊዜ ይኖረናል፡፡

በብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ አልፎ የመጠሪያ ስሙና የመወዳደሪያ ምልክቱ ለሌሎች አካላት ተሰጥተው፣ በአዲስ ስም ለመደራጀት ተገዶ ለዛሬ የደረሰውና ይህ መስራች ጉባኤ አዲሱን መጠሪያ እንደሚያፀድቅለት የሚጠበቀው ፓርቲያችን ያለፈ ታሪኩ በረዥሙ ከተወሳ ወደ ተናጠል ፓርቲዎች ይወስደናል፡፡ ይህን ለጊዜና ለታሪክ ትተን ዛሬ የሚታየው የፓርቲያችን ቅርጽ ከተፈጠረበትና አላማና ፕሮግራሙ ከተቀረፀበት ወቅት ስንጀምር ደግሞ ወደ ህዳር 9 ቀን 1997 ዓም እንሄዳለን፡፡

የግንቦት 1997ቱ ምርጫ እንደ ቀደምት ምርጫዎች ለገዢው ፓርቲ ብቻ የሚቴው ወይንም ለተሳትፎ ብቻ የሚወዳደሩበት ሊሆን እንደማይገባ በብዙዎች ዘንድ የታመነበት ቢሆንም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ካለፈ ስህተታቸው ተምረው ዕርስ በዕርስ ላለመወዳደር የሚያስችላቸውን አንድነት ሳይፈጥሩ የምርጫው ጊዜ እየተቃረበ መምጣቱ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ ነበረ፡፡

በመሆኑም በአደረጃጀታቸው ህብረ-ብሔራዊ የሆኑና የትግል መሠረታቸውን በሀገር ውስጥ አድርገው በተለያየ ጊዜያት የተቋቋሙ አራት ፓርቲዎች ለወራት የዘለቀ ውይይት ሲያደርጉ ቆይተው የአጭር ጊዜ ተግባራቸው በምርጫ 97 አንድ ሆኖ መወዳደርን የረዥም ጊዜ ዕቅዳቸው ደግሞ ከአራትነት ወደ አንድነት መለወጥን አድርገው ህዳር 9 ቀን 1997 ዓም ቅንጅትን በጥምረት መመሥረታቸው ይታወሳል፡፡

ቅንጅት የተመሠረተው ምርጫው አምስት ወራት ብቻ በቀሩበት ጊዜ መሆኑ፣ የአራት ፓርቲ ተወካዮች የተለያዩ ፍላጎቶች ከሚያሳድሩት ተጽዕኖ ጋር ተዳምሮ ም/ቤቱና ሥራ አስፈፃሚው ተለያይተው እንደየኃላፊነት ድርሻቸው መሥራት የሚያስችላቸው ጊዜም ምቹ ሁናቴም ባለማግኘታቸው አብዛኛውን ሥራ ያከናወኑት ሁለቱም አካላት እንደ ሥራ አስፈፃሚ በመሥራት ነበረ፡፡

አራቱ ኮሚቴዎችም በሰው ኃይል ራሳቸውን አደራጅተው ለመሥራት የሚያስችል የዝግጅት ጊዜ ባለማግኘታቸው በአብዛኛው ሥራዎች የተሠሩት በየኮሚቴዎች ውስጥ በነበሩ ከልብ ለውጤት በሚሠሩ ሰዎች የተናጠል ጥረት ነበረ፡፡ ከነበረው የጊዜ እጥረት ወከባና የሥራ መደራረብ አንፃር ሲመዘን ከዚህ ውጭ ሊሰራ ይቻል ነበር ብሎ መደምደምም ተገቢ አይሆንም፡፡

ቅንጅት በምርጫው መካፈልና ለህ/ተ/ም/ቤት 480 ለክልል ም/ቤቶች ደግሞ 600 ያህል ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ማቅረብ መቻሉ እንዲሁም በሂደቱ ንቁ ተሳትፎ ማድረጉና ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር መቀራረብ መፍጠሩ በህዝቡ ልብ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የለውጥ ተስፋን አጫረ፡፡ በምርጫ ተስፋ ቆርጠው የነበሩ በርካታ ሰዎችም በመጨረሻ ሰዓት ተመዝግበው በድምፃቸው ለመወሰን የሚያስችላቸውን ካርድ ለመያዝ በቁ፡፡ ከሀገር ውጭ በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በምርጫው ተስፋ አሳድረው ሂደቱን በቅርብ በመከታተልና የየበኩላቸውን ሁለገብ አስተዋጽኦ በማበርከት የዜግነት ድርሻቸውን አበረከቱ፡፡ አለም አቀፉ ህብረተሰብም ለምርጫው ልዩ ትኩረት በመስጠት ሂደቱን በቅርብ ተከታተለ፡፡

**ክቡራትና ክቡራን !**

ጊዜው እየነጎደና የምርጫው ቀን እየተቃረበ በመጣ መጠን ውስብስብ ችግሮች ማጋጠማቸው አልቀረም፡፡ በአንድ በኩል ሕዝቡ የተመኘውን ለውጥ ሊያስገኝ የሚችል የምርጫ ውጤት ለማምጣት፣ በሌላ በኩል ተፎካካሪያችን ብሸነፍ ምን እሆናለሁ በሚል ስጋት የምርጫውን ሂደት እንዳያበላሸው ማረጋጋት የቅንጅት የወቅቱ ዐቢይ ተግባር ሆኖ ነበር፡፡ ለዚህም በመገናኛ ብዙሃን፣ በክርክር መድረኮች በመስክ እና አዳራሽ ስብሰባዎች በመንገድ ላይ ቅስቀሳዎች በተገቢው

ለመጠቀም ተችሏል። እነዚህ ሁሉ ውጤታማ ተግባራት ሲከናወኑ የምርጫው እለት ከመድረሱ በፊት ጥምረቱን ሊያፈርሱት ይችሉ የነበሩ የውስጥ ችግሮችን በዘዴ ለመያዝ አሰልቺና እልህ አስጨራሽ ሂደቶች ታልፈዋል።

ከየፓርቲዎቹ የተወጣጡ እጩ ተወዳዳሪዎችን በመለየትና በመመደብ ተግባር ላይ ያጋጠሙ ተደጋጋሚና ጥምረቱን ለመፍረስ ሊያበቁ ይችሉ የነበሩ ችግሮች ረዣዥም ሰዓታት በወሰዱና በውጥረት በተሞሉ ስብሰባዎች እየተፈቱ አንድ ወጥ የሆነውን የቅንጅት እጩ ተወዳዳሪዎች ዝርዝር በምርጫ ቦርድ አስመዝግበን የምረጡኝ ዘመቻውንና የቅስቀሳውን ሂደት በአጥጋቢ ሁኔታ እያከናወንን ባለበት ወቅት ይህን ዘመቻ የምናጠናቅቀው «ዴሞክራሲን እናወድስ» በሚል መሪ ቃል ሚያዚያ 30 ቀን 1997 ዓም በመስቀል አደባባይ በሚደረግ የሙዚቃ ዝግጅት መሆኑን ለኢትዮጵያ ህዝብ አበሰርን።

ተፎካካሪያችን ይህን የእኛን ዝግጅት ያደናቀፈ መስሎት ሚያዝያ 29/97 በመስቀል አደባባይ ትእይንተ ህዝብ ጠራ። በእለቱም በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ በአደባባዩ በመገኘቱ መሪዎቹ ስሜታቸውን መቆጣጠር ተስኖአቸው « **ይህ የሕዝብ ማዕበል ያለምንም ማጭበርበር ምርጫውን ማሸነፍ ይችላል**» እስከማለት ደርሰው ነበር።

ይህ ሁኔታ የዴሞክራሲና የነፃነት ተስፋው ያንሰራራውን ህዝብ የለውጥ ፍላጎት ይበልጥ ከፍ አደረገውና የሚያዚያ 30 ቀን 97 ትእይንተ ህዝብ ተካፋይ ለመሆን አበቃው። መስቀል አደባባይ እንኳንስ ሙዚቃ ሊስተጋባበትና ውዳሴ ለዴሞክራሲ ሊገለጽበት ለጠጠር መጣያ ቦታ እስኪጠፋ ድረስ በህዝብ ተጨናነቀ። ከሜክሲኮ አደባባይ እስከ ባምቢስ፣ ከአራት ኪሎ እስከ ጨርቆስ፣ ከቸርችል ጎዳና እስከ ኦሎምፒያ መንገዶች በሙሉ በህዝብ ተጥለቀለቁ።

በዓለም ከታዩ የህዝብ እንቅስቀሴዎች መካከል በግንባር ቀደምትነት ሊመዘገብ የሚበቃው የሚያዚያ 30/97 ትእይንተ ሕዝብ፣ የሕዝቡ ጨዋነትና ህግ አክባሪነት የተረጋገጠበት፣ የለውጥ ፍላጎቱ፣ የዴሞክራሲ ጥማቱና የአገዛዝ ሥርዓት በቃኝ ባይነቱ በግልጽ የታየበት ነበር። ይህ የህዝብ ፍላጎት ወደ ተግባር እንዲለወጥ ማድረግ የቅንጅቱ ከፍተኛ ጭንቀትና ፈተና ነበረ።

ይሁንና በተለያዩ መድረኮችና አጋጣሚዎች ፍላጎቱን የገለፀው በተለይ ደግሞ ሚያዚያ 30 ቀን 1997 እና በተከታዮቹ ቀናት በአዲስ አበባና በየክልሉ ከተሞች አደባባይ ወጥቶ ለቅንጅት ድጋፉን የሰጠውና ግንቦት 7 ከሌሊቱ 10 ሰዓት ጀምሮ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ረዣዥም ሠልፎችን ሠርቶ ያለምንም መታከት ተራውን ጠብቆ በድምጹ የወሰነው ህዝብ የፈለገውን አላገኘ ም። ውሳኔው ሊከበርለትም አልቻለም።

እስከ ድምጽ መስጫው እለት  ድረስ እንከን የለሽ እየተባለ ሲነገርለት የነበረ የምርጫ ሂደት እንከን የበዛበት ለመሆን ጊዜ አልወሰደበትም፣ በተለይም የድምጽ አሰጣጡ ሂደት ገና ሳይጠናቀቅ በጠቅላይ ምኒስትሩ የተሰጠው የአስቸኳይ  ጊዜ መሠል አዋጅ መግለጫ ይህንኑ በውል የሚያስረዳ ነበር:: የዚህ መግለጫ ምንነት በሠፊው እያነጋገረና ሥጋት እያጫረ ባለበት ሰአት የድምጽ ቆጠራ ሂደቱ ገና ሳይጠናቀቅ ገዢው ፓርቲ በሀገር አቀፍ ደረጃ አሸንፌአለሁ በማለት መግለጫ መስጠቱ የምርጫው ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ አቅጣጫውን እንዲለውጥ  የአደረገው ሆነ::

ክቡራትና ክቡራን!

ከምርጫው ውጤት ጋር በተያያዘ በተፈጠሩት ችግሮች የህዝቡ ውሳኔ ያለመከበሩና የለውጥ ፍላጎቱ መጨለሙ፣ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው ዴሞክራሲያዊ ሂደት መደናቀፉ፣ በህይወትና በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱና እነዚህን ተከትሎ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ የሥነ-ልቦና ጫና መፈጠሩ ከልብ አሳዝኖናል:: እኛም እነዛ የዛሬዋን ቀን ለማየት ያልበቁ ወገኖች መስዋእት የሆኑለትን ዴሞክራሲ በዚህች ሀገር እውን የማድረግ ትልቅ ኃላፊነትና ከባድ አደራ አለብን:: ይህንኑ አደራም እንድንጠብቅ መስዋእትነታቸው ግድ ይለናል::

ምርጫ ለቅንጅት  ከሕዝብ በሚገኝ  ይሁንታ በህግ ለተወሰነ ጊዜ  ኃላፊነት የሚረከቡበትና የህዝብ ውሳኔ ወደ ትክክለኛ ሥልጣን የሚቀየርበት ሂደት ነው:: ይህም በመሆኑ ነው በተለይ በመነሻው ወቅት ከሥልጣኑ ይልቅ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመስረት ሲባል ወሳኝ በሆኑ ተቋማት ግንባታ ላይ በማተኮር ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ አማራጮችን ለማቅረብ የተሞከረው:: ፓርላማ ከመግባት ያለመግባት ጉዳይ ጋር ተያይዘው የተነሱት ስምንቱ ጥያቄዎቻችንም በዚህ መሠረተ ሃሣብ ላይ የቆሙ ናቸው:: እነዚህን ጥረቶቻችንን ለማሳካት  በሀገር ሽማግሌዎችና በአለም አቀፉ ማህበረሰብ  የተካሄዱ በጎ ጅምሮች መክሸፋቸው የሂደቱን አቅጣጫ ካስለወጡ አሳዛኝ ድርጊቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው::

የምርጫውን ውጤት ተከትሎ የተፈጠሩ ችግሮች የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ ሂደት በማያደናቅፍ መልኩ መፍትሔ እንዲያገኙ መጣር ዋነኛውና ፋታ የማይሰጠው የወቅቱ ተግባር ቢሆንም ከዚህ ጎን ለጎን የቅንጅትን ሁለተኛውንና  ለትግሉ ይበልጥ ጥንካሬ የሚሰጠውን ውህደት ለማሳካት  የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነው የውህደቱ ጉባኤ መስከረም 14/1998 ዓም ተካሄደ::

ክቡራትና ክቡራን!

ከአራቱ ተጣማሪ ፓርቲዎች ተውጣጥቶ በመስከረም 14ቱ ጉባኤ ይሁንታ ያገኘው 60 የም/ቤት አባላትና 20 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት የነበሩት አመራር የጥምረቱን ሂደት ፈትሾ

ራሱን እቅድ አውጥቶና የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ሥራውን ለመጀመር የሚያስችል ጊዜ ሳያገኝ ከጥምረቱ በተረከባቸው የምርጫ ችግሮች ታስሮ ተያዘ፡፡

በግትር አቋምና በይዋጣልን ስሜት ነገሮች ተካረው አላስፈላጊ ችግሮች እንዳይፈጠሩ በመስጋት ይልቁንም ለዘላቂ ሐገራዊ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠትና ነገሮች ሁሉ በሠላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኙ ካለን ጽኑ ፍላጎት ከህብረት ጋር በጋራ የጠራነውን የመስከረም 22/98 ህዝባዊ ጥሪ ሠረዝን ከገዢው ፓርቲ ጋር ድርድር ለማድረግ ቢሞከርም እኔ በምፈልገው አጀንዳ ላይ ብቻ እንነጋገር የሚል አቋም በገዢው ፓርቲ በመያዙ ድርድሩ ሳይጀመር ሊደናቀፍ በቃ፡፡ ከዚህም በኂላ ቢሆን ተስፋ ባለመቁረጥ የመደራደሪያ መንገዶችን ለማስከፈት የተለያዩ አማራጮች ቢቀርቡም መንግሥት በአማራጮቹ ዙሪያ ለመነጋገር ከመፍቀድ ይልቅ የተለያዩ የኃይል ርምጃዎችን እንደመፍትሔ ተጠቀመ፡፡

መስከረም 14 ቀን 1998 ዓም የተመረጠው አመራር የምርጫው ውጤት ያስከተላቸው ችግሮች በሠላማዊ ሁኔታ መፍትሔ የሚያገኙበትን መንገድ እያፈላለገ ውህዱን ፓርቲ የማስመዝገብ ሥራም ያከናውን ነበረ፡፡ ይህ ተግባር ግን በአመራር ላይ በነበሩ ጥቂት ሰዎች አማካኝነት የገጠመው እንቅፋት ቅንጅት የሚለውን ስያሜ እንዳናገኝ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ነበረ፡፡ በዚህም ምክንያት የውህዱ ፓርቲ ምዝገባ ዘገየ፡፡ ፓርቲውን የማስመዝገብ ሥራ ከዳር ሳያደርስም አመራሩ ለእስራት ተዳረገ፡፡

**ክቡራትና ክቡራን!**

ዴሞክራሲ በተሰበከባት ኢትዮጵያ የተፈፀመው እስራት ከአተገባበሩ አኳያ ብዙዎቹን ያስገረመ ነበር፡፡ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ በ1 ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከሰባ ሺህ እስከ መቶ ሺህ የተገመቱ ዜጎች ወጣት፣ አዛውንት፣ ሴት፣ ወንድ ሳይባል ከየቤታቸው እየተያዙ በግልጽ በሚታወቁም በማይታወቁም እስር ቤቶች ታጎሩ፡፡ ብዙዎቹ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ በደል ተፈፀመባቸው፡፡ ራሱ መንግሥት ባቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን የተረጋገጠ 193 ዜጎች በፀጥታ ኃይሎች ተገደሉ፡፡

የፓርቲ አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎችን የሲቪክ ማህበራት መሪዎችንና ጋዜጠኞችን እንዲሁም ኑሮዋቸው በውጭ ሀገር የሆኑና የተለያዩ ሀገራት ዜግነት ያላቸውን ሰዎች በአንድ ባጠቃለለው የክስ መዝገብ በተከሰሱ ተከሳሾች ላይ እጅግ ዘግናኝ የሆነና የሀገራችንን የፍትህ ታሪክ የሚያጎድፍ የዘር ማጥፋት ክስ ተመስርቶባቸው የሞት ቅጣት ተጠየቀባቸው፡፡

ተከሳሾቹም የክሱን ፖለቲካዊ ይዘት ገልፀው የፖለቲካ ጉዳይ በፍ/ቤት ሊዳኝ እንደማይችል ይዳኝም ቢባል ነፃ ዳኝነት ሊኖር እንደማይችል አስረድተው ምንም አይነት ክርክር እንደማያደርጉና

የሚሰጣቸውን ውሳኔ ለመቀበል ዝግጁ መሆናቸውን በመግለጽ የፀና አቋም ያዙ፡፡ የተለያዩ አለም አቀፍ የሰብአዊ  መብት ተሟጋች ድርጅቶችም የህሊና እስረኞች ናቸው  በማለት ያወጧቸው መግለጫዎች ተከሳሾች የያዙትን አቋም ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ሆኑ፡፡ በዚህም ምክንያት የፍ/ቤቱ ሂደት አለም አቀፍ ትኩረት አግኝቶ የተለያዩ ሀገራትና ድርጅቶች ችሎቱን የሚከታተሉ ታዛቢዎችን መደቡ፡፡  ቁጥራቸው እጅግ ብዙ የሆኑ የህግ ባለሙያዎችም የተባበረ ኃይል ፈጥረው የሙያና የዜግነት ግዴታቸውን ለመወጣት ለተከሳሾች የሙያ እገዛ ሰጡ፡፡ መንግሥት በዜጎች ላይ የወሰደው መጠነ ሠፊ የኃይል እርምጃ ያሰበውን ውጤት ሊያስገኝለት አልቻለም፡፡ እንዲያውም በሀገር ውስጥ ትግሉን ይበልጥ እንዲስፋፋ አደረገው፡፡ በአለም ዙሪያ ተበታትነው የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንም በታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአንድነት እንዲሠለፉ አበቃቸው፡፡ የአውሮፓ ህብረትም በምርጫ ታዛቢ ቡድኑ የቀረበለትን ምርጫው አለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ አይደለም የሚለውን ሪፖርትና የመንግሥት ኃይሎች በዜጎች ላይ የፈፀሙትን ግድያ ምክንያት በማድረግ ለመንግሥት ይሰጥ የነበረውን ቀጥተኛ የበጀት ድጎማ ሲያቋርጥ የተለያዩ ሀገራትም በየግላቸው በመንግሥት ላይ የተለያዩ እርምጃዎችን ወሰዱ፡፡

ከጠባቡ እስር ቤት ውጭ የነበሩ የፓርቲው አመራር አባላት ውህዱን ፓርቲ የማስመዝገብ ጅምር ሂደት ለማስቀጠል ሲሞክሩ ውህደቱን ከፈፀሙት ፓርቲዎች መካከል አንደኛው ተቃውሞ ስላቀረበ ልንመዘግባችሁ አንችልም የሚል ምላሽ ከም/ቦርድ ተሰጣቸው፡፡ ወቅቱ በጉዳዩ ላይ ለመከራከር የሚቻልበት ስላልነበረ ተቃወመ የተባለውን ፓርቲ በመተው በሦስቱ ፓርቲዎች ምዝገባውን ለማካሄድ ጥያቄ ቢያቀርቡም ከምርጫ ቦርድ የተሰጠው ምላሽ ሦስቱ ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤያቸውን ጠርተው ማስወሰን አለባቸው፣ ጥያቄውም በሦስቱ ፓርቲ ሊቃነ-መናብርት ተፈርሞ መቅረብ አለበት የሚል ሆነ፡፡ የሁለቱ ፓርቲዎች ሊቃነመናብርት  በእስር ቤት የነበሩ በመሆኑ ይህም ሳይቻል ቀረ፡፡ ከዚህ በላይ አልፎ ለመሄድም ሁኔታዎች አልፈቀዱም፡፡

ከዚህ በኋላ የተካሄደው ቅንጅትን የማስመዝገብ ሂደት በአዲስ ፓርቲነት ደረጃ ሲሆን ይህንንም ለማድረግ የተንቀሳቀሱት ወገኖች በመካከላቸው ያለመግባባት ተፈጥሮ ጉዳዩ ፍ/ቤት ከደረሰ በኋላ ስሙ ዛሬ ለሚጠቀምበት ቡድን ሊሰጥ ችሏል፡፡

በሀገር ውስጥ ከእስር ውጪ በነበሩት የአመራር አባላት ትግሉን ማስተባበር እንደማይቻል የተገነዘቡ ከሀገር ውጭ የሚኖሩ የፓርቲው አባላት የግል ተነሳሽነት ወስደው የተፈጠረውን የአመራር ክፍተት ለመሙላት የሚያስችላቸው የቅንጅት ዓለም አቀፍ ኮሚቴ አቋቋሙ፡፡ ማዕከሉን በሰሜን አሜሪካ ያደረገው የዚህ ኮሚቴ አባላት በተቋቋሙ ሰሞን መልካም ተግባራትን ያከናወኑ ቢሆንም ብዙም ርቀው መጓዝ ሳይችሉ በመካከላቸው ልዩነት ተፈጠረ፡፡ ይህም ልዩነት እስካሁን ለዘለቀው ችግር አንድ ምክንያት ሆኗል፡፡

ክቡራትና ክቡራን!

በሌላ በኩል መንግሥት በዚህ ወቅት የገጠመውን የፖለቲካ ውጥረት ለማስተንፈስ ይበጀኛል ብሎ ያሰበው የአዲስ አበባን አስተዳደር በቅንጅት ሥም ተመርጠው ነገር ግን በተናጠል ፓርቲዎች ስም ለመያዝ ፈቃደኛ ሆነው ለተገኙት ማስረከብ ነበር፡፡ ይህ ተግባር ተሣክቶ ቢሆን የአዲስ አበባ ህዝብ በመረጣቸው ወኪሎቹ እየተዳደረ ነው፣ ገዢው ፓርቲም የአዲስ አበባ ሽንፈቱን አምኖ ሠላማዊ የሥልጣን ሽግግር አደረገ ለማለት ነበር አላማው፡፡ ይህ እንዲሳካ የተለያዩ ሀገራት ዲፕሎማቶች በሚያስገርም ሁኔታ ከፍተኛ ድጋፍ ሠጥተዋል፡፡ ይህን እቅድ እንዳይሳካ ያደረጉ አባሎቻችን ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው በዛን ቀውጢ ወቅት የማይቻለውን ሁሉ ችለው የፈፀሙት ተግባር ዛሬ በኩራት እንድንቆም ያስቻለን ነውና ምንጊዜም የዚህ ፓርቲ ባለውለታዎች በመሆናቸው አድናቆታችንን ልንገልጽላቸው ይገባል፡፡

ክቡራትና ክቡራን!

ከፍ/ቤቱ ሂደት ጎን ለጎን የተካሄደውንና በርካታ ወራትን የፈጀው ሽምግልና በታሰበውና ቃል በተገባው መሠረት የተከናወነም ባይሆን ከፍ/ቤቱ ውሳኔ በኋላ ተሳክቶ 71 ያህል እስረኞች በአንድ ቀን ሊፈቱ በቁ፡፡ ከ18 ወራት በላይ በፈጀው በዚህ ባህላዊ የሽምግልና ሂደት ያለመታከት ሠርተው የተሳተፉትን የሀገር ሽማግሌዎች በዚህ አጋጣሚ ላመሠግን እወዳለሁ፡፡ አመራሩ ከእስር ቤት ሲወጣ የነበረው ስሜትና በጋራ ተነጋግሮ የደረሰበት ስምምነት ካለፈው ተምረን ድክመቶቻችንን አርመንና ጥንካሬያችንን አጐልብተን ዓላማዎቻችንን ተፈፃሚ ለማድረግ በአንድነት ጠንክረን መታገል፣ ይፈቱ እያለ በተለያየ መንገድ ሲጮህና በጉጉት ሲጠብቀን ለነበረው ህዝብም ተስፋ የሚፈነጥቅ እንቅስቃሴ ማድረግ አለብን የሚል ነበረ፡፡

ዐርብ ሐምሌ 13 ቀን 1999 ዓም አመራሩ የቃሊቲን እስር ቤት ለቆ ከወጣ በኋላ የመጀመሪያ ስብሰባ የተደረገው ሰኞ ሐምሌ 16 ቀን 1999 ዓም ከሰዓት በኋላ ሲሆን የቅድሚያ ተግባሩም አጭር መልዕክት ለህዝብ የተላለፈበትን መግለጫ ማውጣት ነበር፡፡ በዚህ መግለጫም የእስሩና ከእስር የተወጣበትን ሁኔታ በአጭሩ ተገልፆአል፡፡ አመራሩ ቀደም ሲል በያዛቸው አቋሞቹ ፀንቶ እንደሚታገልም አረጋግጧል፡፡ በሀገር ውስጥና በመላው አለም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ እንዲሁም አለማቀፉ ህብረተሰብ ለአደረጉት አስተዋጽኦ ምስጋናውን አቅርቧል፡፡ ቀሪ እስረኞችን ለማስፈታት የሀገር ሽማግሌዎቹ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩም አደራ ብሏል፡፡ ከዚሁ እለት ጀምሮ በተከታታይ በሣምንቱ ውስጥ በተደረጉ ስብሰባዎች አንዳንድ የልዩነት ምልክቶች መታየት ጀመሩ፡፡ የተነጋገርንበትና የተስማማንበት ጉዳይ መሸርሸርና መፍረስ በመጀመሩ የፍላጎትና የስሜት መለያየት በመካከላችን መኖሩን ተገነዘብን፡፡

መስከረም 14 ቀን 1998 ዓም በተካሄደው ጉባኤ ይሁንታ ያገኙ የም/ቤት አባላት በሙሉ ተሰባስበው ሥራ መጀመር እንዳለባቸው ቢታሰብም በዚህ ዙሪያ የተፈጠረው የሃሳብ ልዩነት ለብዙ ቀናት ከማወያየት አልፎ አከራካሪ ለመሆን በቅቶ ነበር።

ጉዳዩ ስምምነት አግኝቶ ሁሉም የም/ቤት አባላት ለስብሰባ የሚጠሩበትን ሁኔታ ለመፍጠር የሚያስችል ውይይት እየተካሄደ በወቅቱ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ መሠራት ያለባቸውና ሊሠሩም የሚችሉ ተግባራትን በመለየት፣ በሀገር ውስጥ ህጋዊነትን የማረጋገጥ፣ የእስረኞችን ጉዳይ የመከታተልና ከሽማግሌዎቹ ጋር በመገናኘት የማስፈታት፣ የሟች ቤተሰቦችን ጉዳይ የማወቅ የአባላትን ሁኔታ የማጣራት፣ ቢሮ የማደራጀትና የፋይናንስ ጉዳይን የመከታተል ሥራዎችን ለመስራት የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቋሙ።

ከሀገር ውጭ ደግሞ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙና ለታሣሪዎች መፈታትና ለተደናቀፈው ዴሞክራሲያዊ ሂደት መቀጠል ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉትን ለማመስገን፣ በድጋፍ ሰጪ ኮሚቴ አባላት መካከል የተፈጠሩ ያለመግባባቶችን ለመፍታትና ለማደራጀት፣ የፋይናንስ ድጋፍ ለማሰባሰብና ዲፕሎማሲያዊ ተግባራትን ለማከናወን ወደ ሰሜን አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ ደቡብ አፍሪካ የሚሄዱ የልዑካ ቡድኖች ተመደቡ። በሰሜን አሜሪካ በተለያየ ጊዜና መንገድ የተቋቋሙት ሁለት አካላት አመራሩ ከእስር ቤት ሲወጣ ተልዕኮአቸው ያበቀ መሆኑ ተገልፆ በሊቀመንበሩ ፊርማ ደብዳቤ ተጽፎላቸው አንደኛው ወገን በደብዳቤ የተገለፀለትን ተቀብሎ ተግባራዊ ሲያደርግ ከመነሻው በሊቀመንበሩ ብቸኛ ትዕዛዝ የተቋቋመውና የእሳቸው ድጋፍ ያልተለየው ወገን አልፈረስኩም በሚል ጭቅጭቅ አነሳ። እነዚህ ወገኖች ወደ አሜሪካ የሚሄደውን ቡድን ተቀብለው ተልዕኮውን ሊያስተባብሩ እንደማይችሉ ስለታመነበት ገለልተኛ የሆኑ ሦስት ሰዎች ተመርጠው በሊቀመንበሩ ፊርማ በተፃፈ ደብዳቤ ኃላፊነት ተሰጣቸው።

የልዑካን ቡድኖቹ የሚሄዱበት ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ ሊቀመንበሩ እንዲመሩት ከተመደቡበት የሰሜን አሜሪካው ቡድን ጋር እንደማይሄዱና ቡድኑ ያለ እሳቸው ቢሄድ ተልዕኮው ሊሳካለት እንደማይችል በይፋ ተናገሩ። የዚሁ አይነት መልዕክት የያዘ ደብዳቤም በሊቀመንበሩ ከሚደገፈው ቡድን ከአሜሪካ ለአመራሩ ተላከ። በዚህ ዙሪያ በተደረገ ውይይት ያለ እኔ አይሳካላችሁም መባሉ ተገቢ እንዳልሆነና ጉዞውን ለማራዘምም የሚያበቃ አጥጋቢ ምክንያት ያልቀረበ መሆኑ ታምኖበት የልዑካ ቡድኑ አባላት ጉዞ በታቀደው መሠረት እንዲፈፀም ተወስኖ ተግባራዊ ሆነ።

ከአሜሪካው ቡድን ጋር አልሄድም ብለው የቀሩት ሊቀመንበሩ ቡድኑ በሄደ በሦስተኛው ቀን ወደ አሜሪካ ቢጓዙም ከቡድኑ ጋር ተቀላቅለው የመሪነት ድርሻቸውን ለመወጣት ባለመፍ

ቀዳቸውና ሌሎች ሰዎችን ከአዲስ አበባ አስወስደው የራሳቸውን ፕሮግራም እና አጀንዳ በማውጣት በመሰላቸው መንገድ መቀጠላቸው በተለያዩ ራዲዮ ጣቢያዎችና ሌሎች የዜና አውታሮች ከሰጧቸው ቃለ ምልልሶች ጋር ተዳምሮ ለልዩነቱና ለጉዳዩ አደባባይ መውጣት ጅማሮ ሆኑ።

የአውሮፓው የአሜሪካውና የደቡብ አፍሪካው ልዑካን ተልዕኮአቸውን ሲፈጽሙ የአውስትራሊያው በጉዞ ፈቃድ ያለማግኘት ምክንያት አልተሳካም። የካናዳው ቡድን ውስጥ ከተመደቡት ሰዎች ጋር በተያያዘ ችግር አንድ የቡድኑ አባል ብቻ ሲጓዝ ተጨማሪ ሰው ከአሜሪካው ቡድን አባላት መካከል ሄዶ ተልዕኮውን ለማሳካት ተችሏል።

ከእስር ቤት የወጣው አመራር ከሐምሌ 16 ቀን 1999 ዓም እስከ ጳጉሜ 3 ቀን 1999 ዓም ድረስ ባሉት ጊዜያት 19 ያህል ስብሰባዎችን አድርጎ ከላይ የተገለፁትን በሀገር ቤት ሊከናወኑ ይገባል ያላቸውን ሥራዎች ለመሥራት ሞክሯል። በዚህ ወቅት ቅንጅት የሚለው ስም የሁሉም የቅንጅት ቤተሰቦች የጋራ መጠሪያ እንዲሆንና ሁሉንም በአንድ ጣራ ሥር ለማምጣት በማሰብ በስሙ ውዝግብ ፈጥረው እስከ ፍርድ ቤት ሄደው ከነበሩት ሁለት ወገኖች ጋር ለመነጋገር ተሞክሮ ነበረ። ነገር ግን አንደኛው ወገን ግንኙነቱን ከምር ወስዶ አብሮነት ለመፍጠር በጎ ፈቃደኝነት ባለማሳየቱ ሂደቱ ወዲያውኑ እንዲቆም ተደርጎ ከሁለተኛው ወገን ጋር የቀጠለው ውይይት ሠምሮ እነሆ ዛሬ በአንድነት ለዚህ ጉባኤ መብቃት ችለናል።

ግንኙነቱን ከምር ወስዶ አብሮነቱን ለመፍጠር ከልቡ የተንቀሳቀሰው ይህ ቡድን ምንም እንኳን የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት ውሳኔን በመተላለፍ ወደ ፓርላማ መግባቱ የማይዘነጋ ስህተት ቢሆንም በዚህ ቡድን ውስጥ የተካተቱት በርካታ አባላት በፓርላማ ቆይታቸው በእውነተኛ ተቃዋሚነት መጽናታቸውና ይበጃል ያሉትንም እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መቆየታቸው ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው።

**ክቡራትና ክቡራን!**

የእኛ ፍላጎት የቅንጅት ቤተሰቦች በመሉ ቅንጅት የሚለውን ሥም ብናገኝም አብረን ብናጣም አዲስ አማራጭ የመፈለጉን ሂደት አብረን ለመፈፀም ነበር። በተለያዩ ሀገራት የተሰማራው የልዑካን ቡድን ወደ ሀገር ቤት እንደተመለሰም አዲስ የተፈጠሩትም ሆነ ቀድሞ የነበሩ ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያ በድርጅቱ መድረክ እንፈታቸዋለን ብለን አስበንም ነበረ። ነገር ግን አብዛኛዎቹ የልዑካን አባላት ወደ ሀገር ቤት ሲመለሱ ሊቀመንበሩ አሜሪካ በመቅረታቸውና ከዛም ሆነው ተ/ም/ሊቀመንበሯን ጨምሮ በአምስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የላዕላይ ም/ቤት አባላት ላይ የማገድ ርምጃ በመውሰዳቸው ከዚህ አልፎም ተተኪ ያሉትን ሰው ከእዛው ሆነው በመሾማቸው ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የነበረው ሃሣብ ትልቅ እንቅፋት ገጠመው።

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አባላት በዚህ የሊቀመንበሩ ህገ-ደንብ የተጣለፈ ድርጊት ላይ ለመወያየት ለስብሰባ ወደ ቢሮ ሲሄዱ የቅንጅት ጽህፈት ቤት ነው ብለው ያስቡት የነበረው ግቢ በር ተዘጋባቸው:: በተመሳሳይ ሁኔታ የላዕላይ ምክር ቤቱ አባላት ፓርቲውን በገጠሙትና ህልውናውን በሚፈታተኑ ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር ለስብሰባ ቢሄዱ የግቢው በር ተዘግቶ እንዳይገቡ ተከለከሉ::

በዚህ ሁኔታ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መሰብሰቢያ ቦታ እንኳን አጥቶ ሲንከራተት ጉዳዩ በአሳሰባቸው አንድ ሀገር ወዳድ ቢሮ ለመጠቀም ቢሞክርም የቤቱን ባለቤት ስልክ እየደወሉ በማስፈራራት እንዲለቅ ተደረገ:: ሆቴል ተከራይተን መግለጫ ልንሰጥ የተለያዩ ሆቴሎችን አነጋግረን ከጨረስን በኋላ ህገ-ወጥ ስብሰባ ነው የምታስተናግዱት እያሉ በስልክ በማስፈራራትና ለፖሊስም በመጠቆም እንዳይሳካልን አደረጉ:: የተዘጋጀውንም መግለጫ በጎዳና ላይ ለጋዜጠኞች እንድንሰጥ ተገደድን::

ይህ ሁሉ ሲሆን ነገሮች ባሉበት ቆመው አለመግባባቶች በውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ውይይት ይህም ካልተቻለው በሀገር ልማድ ሽምግልና እንዲፈቱ ለማስቻል በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገራትም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተለያየ ጥረት አድርገዋል፡፡ በእኛም በኩል ፈቃደኝነታችንን ከማሳየት አልፈን እነዚህ ቅን ዜጎች የተያየዙት ጥረት እንዲሳካ የተቻለንን ሁሉ ያደረግን ቢሆንም አንዳቸውም ጥረቶች ለውጤት ባለመብቃታቸው ከልብ አዝነናል:: በዚህ ታሪካዊ ጉባኤ ፊት ጥረቶቻቸው ለውጤት ያልበቁ ቅን ዜጎችን ልናመሠግናቸውና አክብሮታችንን ልንገልጽላቸው ይገባል፡፡ በእኛ በኩል ጉዳዩ በፓርቲው ህገ ደንብና በውይይት እንዲፈታ ካለን ጽኑ እምነት ዜጎች በራስ ተነሳሽነት ላደረጉት የሽምግልና ጥረት ተባባሪ ከመሆንም በላይ በአሜሪካን ሀገር በሚኖሩ ተናግረው ሊደመጡ ይችላሉ ባልናቸው ሰዎች በኩል የሽምግልና ጥረት እንዲጀመር በደብዳቤ እስከመማፀን ደርሰን ነበር::

ይሁንና በሊቀመንበሩ ወደ ሀገር ቤት ያለመመለስ፣ እዛው ባሉበትም ሆነው ለእርቅ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣ እዚህ ሀገር ውስጥ ያሉት ወኪሎቻቸው ደግሞ ያለ እርሳቸው መወሰን የማይችሉ በመሆኑ፣ ጥረቶች ሁሉ ለፍሬ ሊበቁ አልቻሉም::

ከዚህ በኋላ የነበሩት ጊዜያት በጣም ፈታኝ ነበሩ:: ተገናኝቶ የሚወያይበት ቦታ አልነበረውም፣ የላዕላይ ምክር ቤቱ ምልዐተ ጉባኤ ያለመሟላቱም ሌላው ችግር ነበረ:: ከምንም በላይ ችግሮችን በውይይት በመፍታት አንድነትን ለማምጣት የነበረው ተስፋ የጨለመበት ደረጃ ላይ ደረሠ:: ቅንጅት የሚለው ስማችንና የምርጫ መወዳዳሪያ ምልክታችን ባለቤቶች ሌሎች ሆኑ::

በዚህ መልኩ መቀጠል የማይቻል በመሆኑና ሂደቱን መልክ አስይዞ ለመጀመር የላዕላይ ምክር ቤቱ ውሳኔ በማስፈለጉ ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ስብሰባ ተጠርቶ በሦስተኛው በተገኙ አባላት ውሳኔ መተላለፍ እንዳለበት ሥራ አስፈፃሚው ወስኖ ይህንን በተለያየ መንገድ ይፋ አደረገ:: ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ሲብሰባ ጠርቶም በሦስተኛው የላዕላይ ምክር ቤት አባላት ስብሰባ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በተጓደሉ የላዕላይ ም/ቤት አባላት ምትክ እንዲያሟላና የፓርቲውን ህጋዊነት በአዲስ መልክ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አማራጮችን ፈትሾ ለም/ቤቱ እንዲያቀርብ ወሰነ:: ሊቀመንበሩ የፈፀሟቸው ድርጊቶች በሙሉ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጭ የተፈፀሙ ህገ-ወጥና ኢ-ዴሞክራሲያዊ ተግባራት መሆናቸውንም ገልፆ መግለጫ አወጣ::

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ከላዕላይ ም/ቤቱ በተሰጠው ኃላፊነትና መመሪያ መሠረት የተጓደሉ የላዕላይ ም/ቤት አባላትን አሟልቶ የፓርቲውን ህጋዊነት ለማረጋገጥ ያለው ብቸኛ አማራጭ በአዲስ ሥም መመዝገብ እንደሆነ ገልፆ የካቲት 22 ቀን 1999 ዓም ለተጠራው የላዕላይ ምክር ቤት ስብሰባ አቀረበ:: ም/ቤቱም ይህንን ተቀብሎ በማጽደቅ ሥራ አስፈፃሚው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ፓርቲውን በአዲስ ስም ለማስመዝገብ የሚያስችሉ ተግባራትን አጠናቆ መስራች ጉባኤ እንዲጠራና እስከዚያው ድረስም በአስተባባሪ ኮሚቴነት እንዲሠራ ተወሰነ::

**ክቡራትና ክቡራን !**
**የጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች!**

አስተባባሪ ኮሚቴውም የፓርቲውን ህጋዊነት የሚያረጋግጥ ተግባር ለማከናወን የሚያስችሉትን ኮሚቴዎች ማለትም የህዝብ ግንኙነት ንዑስ ኮሚቴን፣ የፊርማ አሰባሳቢና የጠ/ጉባኤ አባላት ጉዳይን ኮሚቴንና የሰነድ ዝግጅት ኮሚቴን አቋቁሞ ሥራውን ጀመረ:: ፊርማ ለማሰባሰብ ለሚደረገው እንቀስቃሴ የፓርቲው ሥም ወደፊት በጠቅላላ ጉባኤ የሚወሰን ሆኖ አሁን የተጀመረውን እንቅስቃሴ አውቃችሁ የትብብር ደብዳቤ ፃፉልን በማለት ለብም/ቦርድ ላቀረብነው ጥያቄ ጥያቄያችሁን ለማስተናገድ በቅድሚያ ስማችሁን ማወቅ አለብን የሚል ምላሽ በመስጠቱ ሰዎች ይሆናል የሚሉትን ስም እንዲጠቁሙ መልዕክት በማሠራጨት በስልክ፣ በኢ-ሜይል ፣በአካል ቢሮ በመምጣት 125 ያህል ስሞች ተጠቆሙ::

አስተባባሪ ኮሚቴው በስሙ ጉዳይ ሠፊ ወይይት ከአደረገ በኂላ ከተጠቆሙት ስሞች መካከል «አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ» በአህጽሮት (አንድነት) የሚለው ስያሜ በሙሉ ድምጽ ተቀባይነት በማግኘቱ ይሄው ለምርጫ ቦርድ ተገልፆ ወደ ፊርማ ማሰባሰብ ተገባ::

ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ማቅረብ የሚጠበቀው ፊርማ 1500 ቢሆንም በአራቱም የሀገሪቱ ማዕዘን በመንቀሳቀስ 6,925 በላይ ፊርማዎች ለማሰባሰብ ተቻለ፡፡ በተጨማሪም የሠነድ ዝግጅት ንዑስ ኮሚቴ ያለፈውን ደንብና ፕሮግራም በመመርመር በተግባር የታዩ ጉድለቶችን በማሟሟላትና አላስፈላጊ የሆኑትን በመቀነስ ለወቅቱ ድርጅታዊ እንቅስቃሴ የሚመጥን ሰነድ አዘጋጅቶ ለሠነዱ መዳበር ገንቢ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ ተብሎ የታመነባቸው ዜጎች እንዲወያዩበት ተደርጓል፡፡ በበለጠ ስፋት ውይይት ቢደረግበት ምርጫችን የነበረ ቢሆንም ሁኔታዎች ከተደረገው በላይ ለመሄድ አላስቻሉንም፡፡ አስተባባሪ ኮሚቴው ከተለያየ አቅጣጫ የቀረቡ ኃሳቦችን በጥልቀት መርምሮ በበኩሉ ሠነዶቹን የመጨረሻ መልክ ከአስያዘ በኋላ ለዚህ ጉባኤ አቅርቧል፡፡ ዛሬ ይህም ጉባኤ እነዚህን ሁለት ሰነዶች እንዲያፀድቅ ይጠበቃል፡፡

**ክቡራትና ክቡራን!**

ትግላችንን ከባድ ጉዟችንን እረፍት የለሽ የሚያደርገው ካነገብነው አላማ ትክክለኛነት በተጨማሪ ትግሉ በአያሌ ኢትዮጵያውያን ደም የቀለመ መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ለዚህ ክቡር አላማ ለድል መብቃት በቅድሚያ በመረጥነው መንገድ ትክክለኛነት ከአመንና ከአሰብነው ግብ እንደሚያደርሰን እርግጠኛ ከሆንን ቀጣዩ ስራ የሚሆነው እንደመንገዱ ባህሪ ለመጓዝ የሚያስችለንን አካላዊና መንፈሳዊ ዝግጅት ማድረግ፣ ድርጅታዊ አቅምን መገንባት፣ ጉዞአችንን በአንድነትና በተሳካሁኔታ ለማካሄድ የሚያስችል መዋቅር መዘርጋት እንዲሁም ከምኞት ባሻገር ለመታገል የቆረጡና ትውልድ ተሻጋሪ ራዕይ የሰነቁ መሪዎችን ማፍራት ይሆናል፡፡

**የተከበራችሁ የጉባኤው ተሳታፊዎች!**

ቀደም ሲል በተገለጸው የፈታኝ ውጣ ውረድ ጎዳና ተጉዘን ወደ ዛሬው ታሪካዊ እለት ደርሰናል፡፡ እስካሁን ድረስ የመጣነው ያለፍንበትን እየቃኘን ነው፡፡ አሁን ከደረስንበት ቦታና ዝግጅት ላይ ቆመን ወደፊት ስንመለከት በተጓዳኝ ወይም በቅደም ተከተል የሚካሄዱ በርካታ ሥራዎች ሲጠብቁን ይታየናል፡፡ ዋና ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ቀደም ሲል ጀምረነው በዛሬው ጉባኤችን አንድ ትልቅ ርምጃ ወደፊት እያስኬድን ያለነውንና ለድርጅታችን ሕጋዊ ሰውነት ለማስገኘት የሚያስችለውን ሂደት ማሟላት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአዲስ ስም፣ በታደሠ መንፈስ፣ ተደራጅተን ለመንቀሳቀስ የወሰንን መሆናችንን ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም ህብረተሰብ አሳውቀናል፡፡ የመሥራች አባሎቻችንን ስምና ፊርማ አዘጋጅተናል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸው ሰነዶችም ተዘጋጅተዋል፡፡ ዛሬ ጉባኤ እያካሄድን ነው፡፡ የዚህ ጉባኤ ዴሞክራሲያዊ ሂደትና ውሳኔ የሚያርፍባቸው ሠነዶች ለአቀረብነው ጥያቄ ወሳኝ ማሚያዎች ይሆናሉ፡፡

ፓርቲያችን ሕጋዊ እውቅናውን ከአገኘ በኋላ ቀጣዩ ሥራ በሕገ-ደንባችን መሠረት የድርጅታችንን መዋቅር ከማዕከል እስከ ዳር መዘርጋት፣ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ አቅም በፈቀደ መጠን ማሟላትና በፕሮግራማችን መሠረት የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅድ በማውጣት መሥራት መጀመርና ራዕያችን እውን ለማድረግ መጣር ነው::

ሌላው የማይታለፍ ጉዳይ ቅንጅት ከተመሠረተበት ከህዳር 9 ቀን 1997 ዓም ጀምሮ ወደ አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ እስከተሸጋገረበት ጊዜ ያለፈበትን ሂደት በቅንነት፣ በግልጽነትና በድፍረት መገምገምና ከጠንካራና ደካማ ጎኖቻችን ተገቢውን ትምህርት መቅሰም ነው::

ቅንጅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ድርጅት እንደነበረ ሁሉ አንድነትም የቅንጅትን ራዕይ፣ ዓላማና መንፈስ የወረሰ የሕዝብ ድርጅት ነው:: ቅንጅት ለሕዝብ የገባውን ቃል አንድነትም ይበልጥ በተጠናከረ መንፈስ ያድሳል፡ ቃሉንም ተግባራዊ ለማድረግ በቁርጠኝነት የሚታገል መሆኑን ይገልፃል::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቀድሞው ቅንጅት ህልውናውን የተፈታተኑ የውስጥና የውጭ ችግሮች ገጥመውታል:: ተስፋ የተጣለበትና ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበት ፓርቲ ለችግር መዳረጉ በሕዝብ ዘንድ ሀዘንን፣ መደናገጥን፣ መበሳጨትን በተወሰነ መጠንም ተስፋ መቁረጥን እንዲሁም የአስተሳሰብና የእይታ ብዥታም ማስከተሉ አልቀረም:: ሆኖም የድርጅቱን ሕገ-ደንብ ባከበሩና በድርጅቱ ዓላማ በፀኑ ብዙሃኑ የአመራር አባላት፣ ብዙሃኑ አባላትና ደጋፊዎች የተፈጠረውን ችግር ተቋቁመው ለዚህ አዲስ ምዕራፍ በቅተናል:: ከቀጣይ ሥራዎቻችን አንዱና ዋናው የደረሰብን የውስጥና የውጭ ችግር በሁላችንም ዘንድ ያስከተለውን ቁስል ማዳን፣ የተፈጠረውን ብዥታ ማጥራት፣ የሕዝቡን ተስፋ መገንባት፣ በሕዝቡና በድርጅቱ መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ለጋራ ዓላማችን ጠንክሮ መሥራት ነው::

ሌላው የሚጠብቀን ዐቢይ ተግባር ከላይ እስከ ታች የሚገኙ የድርጅቱን አባላት አቅም መገንባትና ድርጅቱን ይበልጥ ማጠናከር፣ የወቅቱን የፖለቲካ ሁኔታ መገምገምና ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ የማስፈን ዓላማችንን ለማሳካት ከሌሎች ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር ሠላማዊና ሕገ-መንግሥታዊ በሆነ መንገድ መሥራት የሚቻልበትን ሁኔታ ማጥናትና የሚደረስበትን የጋራ አቋም ተግባራዊ ማድረግ ነው:: ከዚሁ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን ከሚሹ በየትኛውም አህጉር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር ሀገር ውስጥ ለሚካሄደው ሠላማዊና ሕገ-መንግሥታዊ ትግል አጋዥ ኃይል ሊሆኑ የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሌላው የሚጠብቀን ሥራ ነው::

የሰው ልጅ በረጅም ጊዜ የፖለቲካ ልምዱ የተሻለ ሆኖ ያገኘው የአስተዳደርና የፖለቲካ ሥርዓት ዴሞክራሲ ነው። ዴሞክራሲን ለማስፈን የሚደረገው ትግል ዓለም አቀፋዊ ነው። ይህን ትግላቸውን ቀደም ብለው የጀመሩ ሀገሮች የከፈሉትን መስዋዕትነት ከፍለው የዳበረ የፖለቲካ ባህል ገንብተው የሥርዓቱ ተጠቃሚ በመሆን ላይ ይገኛሉ። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የትግሉ ጀማሪ ሀገሮች ደግሞ ሥርዓቱን በሀገራቸው ለማስፈን በመታገል ላይ ይገኛሉ። እነዚህ ጀማሪ ሀገሮች ከነባር የዴሞክራሲ  ሀገሮች ብዙ የሚማሩት ነገር አለ። ከዚህ አንፃር አንድነት ራሱን ለዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ለማሳወቅና ከግንኙነቱ ተጠቃሚ ለመሆን ብዙ ሥራ ይጠብቀዋል።

ለህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት መረጋገጥ እና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን መሆን ራሱን ብቃት እንዳለው አማራጭ ያቀረበው ፓርቲያችን እንደ ድርጅት ባሳለፍነው ውጣውረድ በተለይም በገጠመን ውስጠ ፓርቲ ችግሮች በድርጅቱ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ አሠራርን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ ብዙ እንደሚቀረው ተገንዝበናል።

ይህ ጉድለት በአለበት ሁኔታ ደግሞ ሥልጣን ቢያዝ እንኳን ድርጅቱ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ስለማድረጉ ምንም አይነት  ዋስትና አይኖርም። ስለሆነም ፓርቲያችን በቀጣይ አመታት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራቸው ተግባራት አንዱ ደንቡን ተከትሎ ፓርቲውን ከላይ እስከታች ማዋቀር፣ በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አካላት እንቅስቃሴዎችም መሠረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎችን እና የህግ የበላይነትን የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ ይሆናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የፓርቲያችን አባላት ለተሻለችው ኢትዮጵያ  አማራጭ የሆነውን የድርጅታችንን የፖለቲካ ፕሮግራምና መተዳደሪያ  ደንብ በአግባቡ የተረዱ፣ የፓርቲውን አላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት ጽናትን የተላበሱ እንዲሆኑ አስፈላጊ የሆኑ የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴዎች ይደረጋሉ።

የፓርቲያችን መለያ ቀለም ከሆኑት የፖለቲካ እምነቶቻችን አንዱ ህብረ-ብሔራዊነት መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ማንኛውም አካለመጠን ያደረሰ ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፓርቲው አላማ እና ራእይ ዙሪያ ለመደራጀት እስከ ወደደ ድረስ የዚህኛው ወይም የዚያኛው ብሔረሰብ አባል መሆኑ ከቁጥር ሳይገባ  በፓርቲያችን ውስጥ የመሳተፍ መብት ያለው መሆኑ በጽኑ የምንቀበለው ሀቅ ነው። እስከአሁን በሄድንበት ጉዞ ከዚህ አንፃር ያየነው ሁኔታ የሚያበረታታ ቢሆንም የፓርቲያችን መዋቅር የማይነካው አንድም የሀገሪቷ ክፍል እና የማያቅፈው አንድም የሀገሪቷ ብሔረሰብ እንዳይኖር ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሊደረግ ይገባል።

በተያያዘም የድርጅታችንን ዴሞክራሲያዊነት እና አሳታፊነት ለማረጋገጥ፣ ለድርጅታችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስኬት ምትክ የለሽ የሆነው የሴቶች እና የወጣቶች ተሳትፎ በሁሉም የፓርቲው እርከኖች እንዲጎለብት ራሱን በቻለ ፖሊሲ የሚመራ ሥራ ከፓርቲው ይጠበቃል፡፡

ሁላችንም እንደምናወቀው በ1997 ዓም የተደረገውን የሀገራችንን ምርጫ ታሪካዊ ከሚያደርጉት ኩነቶች አንዱ ምንአልባትም ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥትን በሠላማዊ መንገድ በህዝብ ድምጽ መለወጥ ይቻላል የሚል ትልቅ እምነት በስፋት የተያዘበት ወቅት መሆኑ ነው፡፡

ይሁን እንጅ ከምርጫው ማግስት ጀምሮ በድምጽ መስጫ ኮሮጆ ዙሪያ ህዝብ ላነሳው ምክንያታዊ እና ህጋዊ ጥያቄ የኃይል ምላሽ በመሰጠቱ በቀጣይነትም የተቃውሞውን የፖለቲካ ሜዳ አለመጠን የሚያጠቡ እንቅስቃሴዎች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ገዢው ፓርቲ በመሰማራቱና ይህን መሰል ውጤት የሚኖራቸው ህጎችን (የፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፣ በረቂቅ ደረጃ የሚገኙ የፕሬስ እንዲሁም የሲቪል ማህበራት አዋጆች ተጠቃሾች ናቸው) አከታትሎ በማውጣቱ የፖለቲካ ራዕያችንን እውን ለማድረግ እና አላማችንን ለማሳካት የተመረጠው የሠላማዊ ትግል ስልት ላይ ጥያቄዎች መነሳታቸው አልቀረም፡፡

በመሠረቱ ሠላማዊ ትግል በገዢው በጎ ፈቃድ ላይ የሚመሠረት እንቅስቀሴ አይደለም፡፡ ይልቁንም ዜጎችን በፖለቲካ ፍላጎታቸው እና በጋራ አመለካከታቸው ዙሪያ አደራጅቶ በህገመንግሥት የታወቁላቸውን መብቶች በመጠቀም የተጠናከረ የጋራ ትግል አድርገው የገዢውን ፍላጎት በማስለወጥ ብሎም በማስገደድ በሕግና በሞራል ኃይል የሚፈለገውን የፖለቲካ ለውጥ በሠላማዊ ሁኔታ ለማምጣት የሚያስችል አስተማማኝ መንገድ ነው፡፡

በመሆኑም ፓርቲው ራሱን ወደተሻለ ድርጅታዊ ጥንካሬ፣ አባላቱን ደግሞ ወደተሻለ የፖለቲካ ንቃት እስካሸጋገረ ድረስ በሠላማዊ ትግሉ ወሳኝነት የሚኖረው የፖለቲካ ስኬት የማግኘት እድሉ ዛሬም በእጃችን ነው፡፡ ከምንም ነገር በላይ በሠላማዊ ትግሉ እስካሁን ምላሽ ላላገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ለሚደረገው ትግል ህዝቡ የትግሉም የሥልጣኑም ባለቤት የሚሆንበት ሂደት እና ውጤት ለመኖሩ ዋስትና የሚሰጥ ስልት በመሆኑ ፓርቲው የተጀመረውን የሠላማዊ ትግል አጠናክሮ የሚቀጥልበት ይሆናል፡፡

ክቡራትና እና ክቡራን!

በዚህ ሪፖርት ለማመላከት እንደተሞከረው በፓርቲያችን የአጭር ጊዜ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ ፖለቲካዊ ድሎችን አስመዝግበናል፡፡ በአንፃሩም ውስብስብ የሆኑ የውስጥ እና የውጭ ችግሮችንም

አልፈናል፡፡ በሂደቱም ከቀሰምነው ትምህርት በመነሳት የድርጅቱ የወደፊት እንቅስቃሴ ምን መልክ ሊኖረው እንደሚችል ከላይ በመጡኑ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

ይሁን እና የትግሉ ዋነኛ ሞተር የሆነው የህዝብ ተሳትፎ ይህን የድርጅቱን እንቅስቃሴ በሀዲዱ ላይ እስከአላሽከረከረው ድረስ የሚኖረው እመርታ እዚህ ግባ የሚባል እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ አጋጣሚ ፓርቲያችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን የሆነባት የበለፀገች ኢትዮጵያን ለማየት ያለመው ራዕይ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የፓርቲውን እንቅስቃሴ በሚችለው ሁሉ እንዲያግዝ ጥሪ አደርጋለሁ፡፡

የድርጅቱም አባላት ፓርቲው የተነሳበት አላማ ዛሬም ሊታገሉለትና መስዋዕትነት ሊከፍሉለት የሚገባ ክቡር አላማ መሆኑን በአጽንኦት በመገንዘብ ዴሞክራሲያዊነት፣ ግልጽነት እና ተጠያቂነት የሠፈነበት የጋራ መታገያ የሆነ ጠንካራ ድርጅት ለመገንባት አስፈላጊውን ሁሉ ሊፈጽሙ እንደሚገባ ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

አመሠግናለሁ፡፡

ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓም